## ክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት የቢዝነስ ሩጫው ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳሰቡ



የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የዴሬክተሮች ቦርድ አባላት ከክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ጋር በብሄራዊ ቤተመንግስት ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓም ውይይት አካሄዱ፡፡

በውይይቱ ላይ የምክር ቤቱን ፕሬዚደንት ጨምሮ የቦርድ አባላት እና የጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች የተገኙ ሲሆን በምክር ቤቱ ባለፉት ሶስት ወራት የተከናወኑ አበይት ስራዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

በዋንኛነትም፤ የንግዱ ኅብረተሰብ በምክር ቤቱ አስተባባሪነት ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ያካሄደው ውይይት እና ከዚያ በማስከተል እየተከናወኑ ባሉ አበይት ስራዎች ዙሪያ፤ ምክር ቤቱ የዓለም ንግድ ምክር ቤቶችን ኮንፍረንስ ለማስተናገድ እያደረገው ስላለው እንቅስቃሴ፤ የምክር ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ማሻሻያ ስላለበት ደረጃ፤ የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በአለም ባንክ የፋይናንስ ድጋፍ አማካኝነት በወተት ልማት፣ ዶሮ እርባታ እና መኖ ማቀነባበሪያ ዘርፎች ዙሪያ የሚያጋጥሙ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውን አስመልክቶ ያዘጋጀውን የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምክከር መድረክ ፣ 2ኛው የቢዝነስ ሩጫ ዝግጅት እና የተለያዩ አንኳር ስራዎችን በተመለከተ የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢኒጂነር መልአኩ እዘዘው ገለጻ አቅርበዋል፡፡

በማስከተልም ትኩረት የሚሹ ተጨማሪ ጉዳዮችን በተመለከተም የዴሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የምክር ቤቱ ዋና ጸኃፊ አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን በዋንኛነትም በአገራዊ ጉዳዮች በሁሉም ዘርፎች በሚደረገው እንክስቃሴ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲጠናከር ከክቡር ፕሬዚደንት አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግ፤ ምክር ቤቱ የራሱ የሆነ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እንዲኖረው ለማስቻል የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ስለመሆኑ ተገልጾ በዚህ በኩል ክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት አስፈላጊ ድጋፍ እንዲያደርጉ፤ የክልል መንግስታት እና የየክልሎች የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ግንኙነትን ለማሳደግ ከክቡር ፕሬዚደንት እገዛ እንደሚፈለግ፤ ምክር ቤቱ ለኤግዚቢሽን እና የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችለውን ህንጻ ለመገንባት እንዲቻለው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጠየቀው ቦታ ፈጣን ምላሽ እንዲያገኝ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ እገዛ እንደሚያስፈልግ በዝርዝር ተነስቶ ክቡር ፕሬዚደንቱ አስፈላጊውን እገዛ እና ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም በአስመጪና ላኪ ዘርፍ ከውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ጀምሮ ሰፊ ችግሮች እንደሚስተዋሉ እንዲሁም ከግብር እና ታክስ ጋር የተያያዙ ክፍተቶችን ለመቅረፍ በሚከናወኑ ስራዎች ዙሪያ ሰፊ ስራዎች እንደሚጠይቁ እና ምክር ቤቱም በነዚህ የግሉ ዘርፍ ሳንካዎች ላይ የተለያዩ ስራዎች እያከናወነ ስለመሆኑ ተነስቷል፡፡

በምክር ቤቱ የተካናወኑ ስራዎች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የስራ መመሪያ የሰጡት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ምክር ቤቱ ድጋፍ በጠየቀባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚሰጡ አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም ሰኔ 10 ቀን 2010 ዓ.ም. በምክር ቤቱ አዘጋጅነት የሚካሄደው 2ኛው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ የግሉ ዘርፍ ወደ ማኒፋክቸሪንግ ዘርፉ እንዲገባ ግንዛቤን ከማስጨበጥ ባሻገር በአረንጓዴ ልማት ዙሪያ ግንዛቤን የሚያሳድግ መድረክ በመሆኑ ለወደፊቱ ተጠናክሮ ሊካሄድ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡ ቀድሞ በተያዘ መንግስታዊ ፕሮግራም ምክንያት በዕለቱ ለመገኘት ባይችሉም ‹‹**እኔም ከእናንተ ጋር በመንፈስ እሮጣለው**›› ብለዋል፡፡

ክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የበላይ ጠባቂ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

## የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምከከር መድረክ ውይይት ተካሄደ

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር *በአለም ባንክ የፋይናንስ ድጋፍ አማካኝነት በወተት ልማት፣ ዶሮ እርባታ እና መኖ ማቀነባበሪያ ዘርፎች ዙሪያ የሚያጋጥሙ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ላይ የተዘጋጀ* የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምከከር መድረክ ውይይት ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም በሂልተን ሆቴል አካሄደ::



የግብርና እና እንስሳት ሃብት ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ፕሮፌሰር ፈቃዱ በየነ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት በኢትዮጵያ የእንሰሳት ዘርፍ ከአነስተኛ ይዞታ አርብቶ/አርሶ አደሮች የምግብ ዋስትና ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ድረስ ያለው ሚና ቀላል የሚባል ባይሆንም የኢኮኖሚያዊ መዋቅር ሽግግር በማረጋገጥ ረገድ የተገኘው ውጤት ግን የሚጠበቀዉን ያህል ባለመሆኑ ችግሮቹን ለይቶ በማወቅ ለመፍትሄው የተሻለ ቅንጅታዊ ስራ ይጠይቃል፡፡

ይህን በመሰሉ የጥናት ውጤቶችና የውይይት መድረኮች ላይ መወያየት ችግሮችን ከመረዳት ባሻገር ለመግባባትና ተረዳድቶ ወደ አንድ የጋራ ግብ ለመድረስ ስለሚያስችል ሊዘወተርና ሊበረታታ እንደሚገባ ሚኒስትር ደኤታው አክለው ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) በበኩላቸው እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ምንም ያህል ከፍተኛ የእንስሳት ቁጥር፣ የተመቸ መልክአ-ምድራዊና የአየር ሁኔታ ቢኖርም ከእንሰሳት ሀብት እየተገኘ ያለው ውጤት ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ በጥናት ለይ ተመስርተው በተለዩ የዘርፉ ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ መወያየት ለነገ የማይባል ሥራ ነው፡፡

ፕሬዚደንቱ ጨምረው እንደገለፁት መድረኩ በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች ያሉትን የሥራ አማራጮች እና በመንግሥት በኩል ስለተዘጋጁ ማበረታቻዎች ግንዛቤ እንደሚያስጨብጥም ገልፀዋል፡፡

በእለቱ *በወተት ልማት፣ ዶሮ እርባታ እና መኖ ማቀነባበሪያ ዘርፎች የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ በሚያጋጥሟቸው ችግሮችና የችግሮቹ መንስኤዎች እንዲሁም በመፍትሄዎቻቸው ዙሪያ የተዘጋጀ የአቋም ማንፀባረቂያ ጥናታዊ ፅሁፍ የፓወር ፖይንት ገለፃ ከተደረገ በኋላ በተሳታፊዎች ሰፊ ዉይይት ተደርጎበታል፡፡*

ከውይይቱ በተገኘው ግብዓት መሰረት የጥናቱን ሰነድ የሚያሻሽልና የጥናቱን ውጤት አፈፃፀም የሚከታተል ሰባት አባላት ያለው ግብረ-ሀይልም ተቋቋሚል፡፡

ከፍተኛ የመንግስት ሀላፊዎች፣ የምክር ቤቱ የቦርድ አባላት እና *በዘርፉ የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች፣* እንዲሁም ከአጋር አካላት የመጡ በርካታ ተሳታፊዎች በውይይቱ ላይ ተገኝተዋል።

## አባል ምክር ቤቶች የበለጠ በመቀራረብ አብረው መስራት እንደሚገባቸው ተጠቆመ





የየኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባል ምክር ቤቶችን የሚያሳትፍ የውይይት ፎረም ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም በምክር ቤቱ አዳራሽ አዘጋጀ፡፡

የፎረሙ ዓላማ ተሳታፊዎች የመጡበትን ተቋም ወክለው ያላቸውን የስራ እንቅስቃሴዎች፣ መረጃዎች እና ልምዳቸውን አንዱ ለሌላው በማካፈል፣ እርስ በርስ የሚማማሩበትን እና የሚተዋወቁበትን መድረክ ለመፍጠር ነው፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ እዘዘው እና የምክር ቤቱ ዋና ፀኃፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ ለ12ኛ ጊዜ ስለሚካሄደው አለም ዓቀፍ የንግድ ምክር ቤቶች ጉባኤ፣ የአፍሪካ አህጉር የነፃ ንግድ ቀጠና፣ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረኮች፣የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት፣ የክልል ቢዝነስ አጀንዳዎች፣ ስለ ሁለተኛው የኢትዮጵያ የቢዝነስ ሩጫ፣ በምክር ቤቱ አካዳሚ አማካኝነት ስለተሰጡ ስልጠናዎች እና ሌሎችም በርካታ ዓበይት የንግድና ኢንቨስትመንት ክንውኖች አጠቃላይ ገለፃ አድርገዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት አባል ምክር ቤቶች የበለጠ በመቀራረብ እና አብረው በመስራት የንግዱን ማህበረሰብ ተወዳዳሪነት እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ መዘውር አንቀሳቃሽነት እውነታ እውን ማድረግ እንደሚገባም ተገልጿል፡፡

በፎረሙ ላይ የክልል ንግድ ምክር ቤቶች እና የማህበራት ከፍተኛ አመራሮች፣ የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ እና የማኔጅመንት አባላት የልምድና አጠቃላይ የመረጃ ልዉዉጥ ያደረጉ ሲሆን የምክር ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ለማሻሻል በቀረቡ ሃሳቦች ላይም ተወያይተዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የውይይት መድረክ በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚካሄድ ታውቋል፡፡

# Member Chambers Said to Further Strengthen Ties and Work Together





Organized by the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), Member Chambers Forum was held on May 25, 2018 at Board Room of ECCSA.

The aim of the forum was sharing experience and exchanging information among Member Chambers.

Melaku Ezezew (Eng.), President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), together with Endalkachew Simie, Secretary General of ECCSA, has provided the participants with the general information concerning the 12th World Chambers Congress, African Continent Free Trade Area, Public Private Dialogues, Public Private Partnership, Regional Business Agendas, the 2nd Ethiopian Business Run, capacity buildings and other major activities of trade and investment.

It was said that Member Chambers and ECCSA should strengthen their relationships among themselves and work together in order to make the business communities more competent and realize being the engine of the economy of the country.

On the forum, high ranking officials of the regional chambers and sectoral associations, Members of Board of Directors and Management of ECCSA have shared their vital experiences and information on different issues of their respective chambers and associations and also deliberated on the revised Proclamation No. 341/2003 of the Chamber.

It was learnt that such kind of forum is organized twice per year.

# Public Private Consultative Forum Organized



The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), in partnership with the Ministry of Trade under the support of IFC- member of the World Bank Group, organized a public private consultative forum on the major challenges and solutions of milk, poultry and feed processing areas in Ethiopia on May 24, 2018 at Hilton Addis Hotel.

In his opening remarks, Fekadu Beyene (Prof.), State Minister of Ministry of Agriculture and Livestock, said that although the livestock sector is contributing a lot to the livelihood of the small land holding farmers and other peoples of the country, its capacity to transform the country's economy is very low. The State Minister further said identifying the problems and obtaining solutions of the sector thus demanding combined efforts of the concerned bodies.

Melaku Ezezew (Eng.), President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), on his part stated that since the economic benefits obtained from the livestock sector in Ethiopia is below the expected level, organizing such a consultative forum to discuss the challenges and solutions based on the results of the study was a mandatory. The forum would create awareness to the potential investors who want to engage in the sector about the available opportunities and incentives provided by the government, the President added.

A power point presentation on the root causes, problems and recommended solutions in the businesses related to milk production, poultry farming and feed processing were presented and reflections have been made from both the private sector and the government sides, in the mean time, relevant inputs were identified so as to incorporate to the study.

A task force composed of seven members representing different sectors has also been established to follow up the implementation of the study.

High government officials, members of Board of Directors of ECCSA, representatives from the business communities and stakeholders have participated actively on the forum.